# ድጋፍ፡ ጆ ባይደን ለፕሬዝዳንትነት እና ካማላ ሀሪስ ለምክትል ፕሬዝዳንትነት

***ቮይስ ፎር ሬፍዩጂ ጆ ባይደንን ለፕሬዚዳንትነት ካሚላ ሀሪስን ደግሞ ለምክትል ፕሬዚዳንትነት ድጋፍ ሲሰጥ ከፍተኛ ኩራት ይሰማዋል።***

ለረጅም ዓመታት በዴላዌር በሴናተርነት እንዲሁም በባራክ ኦባማ የስልጣን ዘመን በምክትል ፕሬዚዳንትነት ያገለገሉት የዲሞክራቲክ ፓርቲ ዕጩው ጆ ባይደን ለሕይወታችን እጅግ አስፈላጊ ለሆነው ምርጫ ዕጩ ሆነው ቀርበዋል። **ስደተኞች በፕሬዚዳንት ትራምፕ ከፍተኛ መዋረድ ደርሶባቸዋል፣** በግልጽ ዘረኛና የእስልምና ሀይማኖት ፍራቻ ያለባቸው ትራምፕ ሙስሊሞችን ፣አፍሪካውያንንና ስደተኞችን እጅግ አምርረው ስለሚጠሉ ጥገኝነት ጥየቃን ከመከልከላቸውም በተጨማሪ ከዚህ በፊት የነበረውን የጥገኝነት ቅበላ 80 በመቶ ከመቀነሳቸውም በላይ ሕጻናትን ከወላጆቻቸው በመነጠል ወላጆችን ከድንበር በመመለስ የስደተኞችን መሠረታዊ መብት ጥሰዋል። ይህ ደግሞ ሕግን ከመጣስ ባለፈ ከሰው ልጆች የደግነት ባሕርያት ያፈነገጠ ነው። የስደተኞች ሕይወትና ሰቆቃን አምልጠው የመጡ ሰዎች ደኅንነታቸው ተጠብቆ እንዲኖሩ ማድረግ የሞራል ግዴታ በመሆኑ የትኛውን ዕጩ መደገፍ እንዳለብን የሚጠቁም ነው።

ከትራምፕ በተቃራኒ ጆ ባይደን ስደተኞችን በተመለከተ ያላቸው መልካም ፈቃደኝነትና እንቅስቃሴያቸው ዘመናትን የተሻገረ ነው። በአሜሪካ በ1980 ስደተኞችን መልሶ ስለማቋቋም የጥገኝነት ሥርዓት ፕሮገራም ሲመሰረት ዋና ተሳታፊ ነበሩ[i]። ያ ስሜታቸው ዛሬም ድረስ በውስጣቸው ስላለ የአሜሪካውያንን እንግዳ ተቀባይነት ዳግም ለማምጣትና ለመገንባት ቃል ገብተዋል።

ባይደን ትራምፕ በሙስሊሞች፣ በአፍሪካውያን፣ በስደተኞችና በጥገኝነት ጠያቂዎች ላይ ያወጡትን እገዳ[ii] የሚሽር ሕግ ደጋፊ ከመሆናቸው በላይ አስተዳደራቸው ለጥገኝነት ጠያቂ ቤተሰቦችም[iii] ከለላ የሚሰጥ ይሆናል። ትራምፕ በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የስደተኞች ቅበላ ቁጥርን ወደ 18000 ዝቅ ያደረጉት ሲሆን ባይደን ግን ይህን ቁጥር ወደ 125000 ከፍ እንደሚያደርጉት ቃል ገብተዋል።[iv] ይህ ቅበላ በኦባማ የግዛት ዘመን ከነበረው 111000 አዳዲስ ስደተኞችንና ቤተሰብን የማቀላቀል ሂደት የሚበልጥ ነው።[v]

# በጉዳዮቹ ላይ፡ ጆ ባይደንና ዶናልድ ትራምፕ ሲነጻጸሩ

| ጉዳዩ | ዶናልድ ትራምፕ | ጆ ባይደን |
|---|---|---|
| ስደተኞች ስለማቋቋም | ስደተኞችን ስለማቋቋም ቅበላውን 80 በመቶ በመቀነስ ወደ 18000 ማውረድ የስደተኞች ማቋቋሚያ ፕሮግራምን መሰረዝ፣ ቤተሰብን መለያየትና በአደገኛ ሁኔታ እንዲኖሩ ማድረግ።[vi] | ስደተኞችን አስመልክቶ በ1980 የወጣውን ሕግ ዳግም እንዲሰራ ፕሮግራም በመንደፍ በየዓመቱ 125000 ስደተኞችን ለመቀበል የሚያስችል ፕሮግራም ነድፈዋል።[vii] |
| ሙስሊሞችን ማገድ፣<br>አፍሪካውያንን ማገድ፣<br>ስደተኞችን ማገድ፣<br>ጥገኝነት ጠያቂዎችን ማገድ፣<br>የናሪነት ጥያቄዎችን ማገድ | ሙስሊሞችን፣ አፍሪካውያንን፣ ስደተኞችን ጥገኝነት ጠያቂዎችን ጥያቄዎች በማገድ[viii] ቤተሰቦችን ለያይተዋል። በግልጽ የፍርድ ቤት ትዕዛዞችን ጥሰዋል፣ ተግባራዊ እንዳይሆኑ አድርገዋል። | እነዚህ እገዳዎች ስህተት ስለመሆናቸው ደጋግመው ከመናገራቸው በተጨማሪ እንዲሻሩ አሳስበዋል።[ix] በዚህ መመሪያ ቀጥታ ተጠቂ የሆኑትን የውይይት መድረክ በመምራት ብሶታቸውን አዳምጠዋል። |
| ጥገኝነት ጠያቂ ቤተሰቦችንና ግለሰቦችን በተመለከተ | ከለላ የሚፈልጉትን አባርረዋል፣ ልጆችን ከወላጆች ነጥለዋል፣ ጥገኝነት ጠያቂዎች ደኅንነቱ ባልተጠበቀ ቦታ እንዲቆዩ በማድረጋቸው ለሞት፣[x] ከፍላጎት ውጪ ማምከን፣[xi] እና ለጥቃት ተዳርገዋል። | ጥገኝነት ጠያቂዎችን ይቀበላሉ፣ የተለያዩ ቤተሰቦችን ያገናኛሉ፣ እስር ቤቶችን በተመለከተ ማኅበረሰብ ተኮር አማራጮችን ይጠቀማሉ፣ እንዲሁም በጥገኝነት ጥያቄ ዙሪያ ሥነ-ምግባር የተላበሰ ትክክለኛ ሥርዓት ይዘረጋሉ። |
| የግዛቶችና የአካባቢ የስደተኞች መልሶ ማቋቋም እገዳ | ግዛቶችና አካባቢዎች ስደተኞችን መልሶ ማቋቋሚያ ገንዘብ እንዳያወጡ የሚያግዝ ሕግ ላይ ፈርመዋል። (እንደ እድል ሆኖ ፍርድ ቤቱ ይህንን ለጊዜውም ቢሆን አስቁሞታል)።[xii] | ስደተኞች ላይ የሚደርሰውን መድልዎ በማስወገድ ከግዛቶችና ከአካባቢ አስተዳደሮች ጋር በመተባበር ስደተኞችንና ተቀባዮቹን ይደግፋሉ። |
| ጊዜያዊ ከለላ የማግኘት መብት (TPS) | ከተለያዩ አገራት የመጡ ከ 300 000 በላይ ተጠቃሚዎችን ጊዜያዊ ከለላ በማንሳታቸው በአስጊ ሁኔታ ላይ ወድቀዋል። ምንም እንኳን ፍርድ ቤት ለአንዳንዶቹ ከለላ ማድረጉን ቢቀጥልም ትራምፕ ግን ጊዜያዊ ከለላ ፈላጊዎችን ማጥቃታቸውን ቀጥለዋል። | የጊዜያዊ ከለላ የማግኘት( TPS) እና በግዳጅ የተለያዩ አካላትን መብቶችን (DED)መልሰው ተግባራዊ ያደርጋሉ። በተፈጥሮ እና በሰው ሰራሽ አደጋዎች ቤተሰቦች እንዳይለያዩ የሚያደርጉ ሥርዓቶችን ይደግፋሉ። |
| ተስፈኞችና የሕጻናት ስደተኞች ጉዳይ (DACA) | ፍርድ ቤት የህጻናት ስደተኞች የዳካ ፕሮግራምን እንዲቀጥል ቢያዝም ትራምፕ ግን የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸው ወጣቶችን ወደመጡበት ለመመለስ ፕሮግራሙን ለመዝጋት በመጣር ላይ ናቸው። | የወጣቶችን የጥገኝነት ጥያቄ DACA በመቀበል የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸው ወጣቶች በዩናይትድ ስቴትስ ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲቆዩ ጥበቃዎችን ይዘረጋሉ። |
| ስደተኞችንና ጥገኝነት ጠያቂዎችን አስመልክቶ ስለመናገር | እነዚህን ሰዎች ሁሉ ተቀብለን አገራችንን እንዲወሩ አንፈቅድላቸውም፣ አንድ ሰው ወደአገራችን ከመጣ ያለዳኛና ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወደመጣበት እንመልሰዋለን እንደሚሉ ዓይነት የሰው ልጆችን ክብር ዝቅ የሚያደርግና የሚያጥላሉ ቃላትን ይጠቀማሉ።[xiii] | ስደተኞች የአሜሪካ የጥንካሬ ምንጭ እንደሆኑ ይናገራሉ፡ በዚህ የዓለም የስደተኞች ቀን በአንድነት በመቆም ሌሎችን የምትቀበልና የምታሳትፍ አሜሪካ ለመገንባት ቁርጠኞች መሆን አለብን። የአገራችንን ማንነት መልሰን የምናመጣ በዚህ መንገድ ነው። ብለዋል።[xiv] |
| **ደረጃ** | **አክራሪ ፀረ- ስደተኛ** | **ለስደተኞች ድጋፍ ያለው መሪ** |

# በጉዳዮቹ ላይ፡ ካማላ ሀሪስ እና ማይክ ፔንስ ሲነጻጸሩ

| ጉዳዩ | ማይክ ፔንስ | ካማላ ሀሪስ |
|---|---|---|
| **የስተኞች መልሶ ማቋቋም** | ትራምፕ ያደረጉትን የስደተኞች ቅነሳ ይደግፋሉ፣ በሀይማኖታቸው ምክንያት ስቃይ ደርሶባቸው የተሰደዱትን እንደሚደግፉ ይናገራሉ። ይሁን እንጂ ትራምፕ በአሜሪካ ታሪክ ተጠብቆ የቆዩትን የአናሳዎችን ሀይማኖቶች በመቀነስ ከሌላው ጊዜ የበለጠ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርገዋል።[xv] | ትራምፕ የስደተኞች እገዛ የሚውለውን ገንዘብ በማጥፋታቸው ተቃውመዋል እንዲሁም ብዙ ስደተኞች እንዲመጡ የሚያዘውንና በአብዛኞቹ ሴናተሮች የተፈረመውን ደብዳቤ ጽፈዋል[xvi]። በመጀመሪያው የሴናተርነት ጉዟቸው የሶሪያ ስደተኞችን ጎብኝተዋል።[xvii] |
| **ሙስሊሞችን ማገድ፣<br>አፍሪካውያንን ማገድ፣<br>ስደተኞችን ማገድ፣<br>ጥገኝነት ጠያቂዎችን ማገድ፣<br>የኗሪነት ጥያቄዎችን ማገድ** | ይህንን የትራምፕ ከሥነ-ምግባር የወጣ የውጪ ዜጎችን ጥላቻ ፖሊሲ ይደግፋሉ፣ የገዢነት ስልጣናቸውን ተጠቅመው የሶሪያ ስደተኞችን ከኢንዲያና እንዲወጡ ሙከራ አድርገዋል።[xviii] | ሰብዓዊነት የጎደላቸው እገዳዎችን ይቃወማሉ። እገዳዎቹ እንዲነሱ የሚያደርገውን የባይድን መመሪያ ይደግፋሉ፣ባይደን ከፍጻሜ እንዲያደርሷቸውም ያግዛሉ።[xix] |
| **የስደተኞች ድምጽና ችግር ማዳመጥና ማጉላት** | ትራምፕን ፈለግ በመከተል የተሻለ ኑሮ ፍለጋ የመጡትን ያንቋሽሻሉ፣ ቅሬታዎቻቸውንም አይሰሙም። | የካሊፎርኒያ የጠበቆች ኃላፊ የሴኔት አባል በነበሩ እንደሚያደርጉት የስደተኞችን ቅሬታ ያዳምጣሉ።[xx] |
| **ተስፈኞችና የሕጻናት ስደተኞች ጉዳይ (DACA)** | ከትራምፕ አስተዳደር ጋር በመተባበር ወረቀት የሌላቸውንወጣቶች ከአሜሪካ እንዲወጡ ለሚያዘው ረቂቅሕግ ድምጽ ሰጥተዋል።[xxi] | ጆ ባይደን ዳካን ለማስቀጠል እና ለቤተሰቦቻቸው መከላከያ ለመስጠት እያደረጉት ያለውን ጥረት ይደግፋሉ። |
| **ደረጃ** | **አክራሪ ፀረ- ስደተኛ** | **ለስደተኞች ድጋፍ ያለው መሪ** |

ከጆ ባይደን ጋር በመሆን ለምክትል ፕሬዚደንትነት የሚወዳደሩት ሀሪስ በዋነኝነት የስደተኞች ጉዳይ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ራሳቸው ሀሪስ ከኢንዲያና ከጃማይካ ከመጡ ስደተኛ ወላጆች የተገኙ ስለሆነ ጠበቆች ኃላፊና የአሜሪካ የሴኔት አባል በነበሩበት ወቅት ከምንም እና ከማንም በላይ እሳቸውም ሆኑ ቢሯቸው በስደተኞች ጉዳይ ላይ ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል። ሀሪስ የስደተኞች ድጋፍ ሰልፎች ላይ ይገኙ የነበረ ሲሆን ብዙ ስደተኞችንና ጥገኝነት ጠያቂዎችን በግል በማግኘት በጉዳዩ ላይ በተሻለ መንገድ መነጋገር ስለሚቻልበት መንገድ ይወያዩ ነበር። በተጨማሪም ስደተኞችን የሚደግፍ አምስት ነጥቦችን የያዘው መመሪያ ሲዘጋጅ ከመተባበራቸውም በላይ ትራምፕ ለስደተኞች መልሶ ማቋቋሚያ በጀት መቀነሳቸውን የሚቃወምና ብዙዎቹ የሴኔት አባላት የፈረሙበትን ደብዳቤ ጽፈዋል።[xxii] ሀሪስ ጥገኝነት ጠያቂ ልጆችና አዋቂዎች የህግ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያዘውን መመሪያም ጽፈዋል።[xxiii] እንዲሁም የትራምፕን የሙስሊም፣ የስደተኞችንና የጥገኝነት ጠያቂዎችን ጥላቻና እገዳ በመቃወም አሜሪካ መከራን ፈርተው

ለመጡ ስደተኞች መልካም አቀባበል የማድረግ ኃላፊነት  እንዳለባት በቃላቸውም ሆነ በድርጊታቸው ሲያሳዩ ቆይተዋል።[xxiv]

በተቃራኒው የትራምፕ ምክትል ፕሬዚዳንት ማይክ ፔንስ ስደተኞችን በተመለከተ አሳፋሪ ታሪክ አስመዝግበዋል። እንደ ኢንዲያና ገዢነታቸው የሶሪያ ስደተኞችን የሚከለክል አስተዳደራዊ መመሪያ ፈርመዋል።[xxv] የፌዴራል ዳኝነት ይህን ሁኔታ "ሕገ መንግስቱን በግልጽ የሚቃወምና አድሏዊ ነው" ቢለውም የትራምፕና የፔንስ አስተዳደር ስደተኞችን የማቋቋም ፕሮግራምን ከማገዱ በተጨማሪ በዘረኝነተና በእስልምና ሀይማኖት ጠልነቱ በመግፋቱ በስደተኞቹ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ከማሳረፉም በላይ የጥላቻ ወንጀል እንዲፈጸምባቸው ምክንያት ሆኗል። ፔንስ ትራምፕ ለስተደተኞች የሚወጣውን ገንዘብ መቀነሳቸውን ሙሉ በሙሉ  ይደግፋሉ። በሀይማኖታቸው ምክንያት ስቃይ የደረሰባቸውንም እንደሚደግፉ ይናገራሉ።ይሁን እንጂ ትራምፕ በአሜሪካ ታሪክ ተጠብቀው የቆዩትን የአናሳዎችን ብዙ ሀይማኖቶች ቀንሰዋል። የሀሪስ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆኖ መመረጥ ታዲያ ይህን የፔንስ ፀረ-ስደተኛ አቋም በከፍተኛ ደረጃ ያስቆመዋል። እያንዳንዱ የስደተኞች ደጋፊ በመጪው ምርጫ ለእሳቸውም ሆነ ለባይደን ድጋፉን ሊሰጥ ይገባል።

በእነዚህ ምክንያቶች  ቮይስ ፎር ሬፍዩጂ ባይደንን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሀሪስን ደግሞ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው እንዲመረጡ ድጋፉን ሲሰጥ በታላቅ ኩራት ነው። በኖቬምበር የሚደረገው አገራዊ ምርጫ ለስደተኞች፣ ጥገኝነት ጠያቂዎች፣ ለጥቁሮች፣ ለተወላጆች፣ ለሌሎችም ከለርድ ለተባሉ ሕዝቦች ወሳኝ ነው። የባይድንና የሀሪስ ስኬት ከቦታቸው የተፈናቀሉ ሰዎች ሕይወት ለሚያሳስባቸውን አሜሪካ በውስጥም ሆነ በውጭ በሥነ-ምግባር የታነጸ አስተዳደር እንዳላት ለማየት ለሚጓጉ ድምጽ ሰጪዎች አስተማማኝ ዕጩዎች ስለሆኑ ሁሉም ሕጋዊ መራጭ ድምጹን በኢሜል ወይም በአካል በመቅረብ ሊሰጣቸው ይገባል። መመዝገብዎንና በተቻለ ፍጥነት ለመምረጥ ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ። ለመምረጥ የሚያስፈልጉ ነገሮችን እዚህ ያገኛሉ። ቀጣዩ የስደተኞች እና የዜጎች እጣ-ፈንታ ከፊት ለፊታችን ነው።

---

[i] S.643 - Refugee Act of 1979. congress.gov, <https://www.congress.gov/bill/96th-congress/senate-bill/643/cosponsors?searchResultViewType=expanded>.

[ii] Joe Biden, My Statement on World Refugee Day. Medium, 06/20/2020. <https://medium.com/@JoeBiden/my-statement-on-world-refugee-day-fddb4abddfd5>.

[iii] The Biden Plan for Securing Our Values as a Nation of Immigrants. Biden for President, 2020. <https://joebiden.com/immigration/>.

[iv] Dahlia Lithwick, How Biden Plans to Undo Trump's Nativist Agenda. The Slate Group, 06/29/2020. <https://slate.com/news-and-politics/2020/06/biden-refugee-plan.html>.

[v] Barack Obama, Presidential Determination -- Refugee Admissions for Fiscal Year 2017. The White House, 09/28/2016. <https://obamawhitehouse.archives.gov/the-press-office/2016/09/28/presidential-determination-refugee-admissions-fiscal-year-2017>.

[vi] "U.S. Annual Refugee Resettlement Ceilings and Number of Refugees Admitted, 1980-Present." The Migration Policy Institute. <https://www.migrationpolicy.org/programs/data-hub/charts/us-annual-refugee-resettlement-ceilings-and-number-refugees-admitted-united>.

[vii] "The Biden Plan for Securing Our Values as a National of Immigrants." <https://joebiden.com/immigration/>.

[viii] Timeline of the Muslim Ban. ACLU. <https://www.aclu-wa.org/pages/timeline-muslim-ban>.

[ix] "Biden pledges to end Trump's 'Muslim ban' on his first day in office." <https://www.cnbc.com/2020/07/20/biden-pledges-to-end-trumps-muslim-ban-on-his-first-day-in-office.html>.

[x] "Deaths at Adult Detention Centers." <https://www.aila.org/infonet/deaths-at-adult-detention-centers>.

[xi] "Whistleblower Alleges 'Medical Neglect,' Questionable Hysterectomies Of ICE Detainees." <https://www.npr.org/2020/09/16/913398383/whistleblower-alleges-medical-neglect-questionable-hysterectomies-of-ice-detaine>.

[xii] “Judge Blocks Trump's Executive Order Allowing Local Officials To Reject Refugees.” <https://www.npr.org/2020/01/15/796658527/judge-blocks-trumps-executive-order-allowing-local-officials-to-reject-refugees>.

[xiii] Donald Trump, Twitter, Inc., 10/29/2018. <https://twitter.com/realdonaldtrump/status/1010900865602019329?lang=en>.

[xiv] Joe Biden, “My Statement on World Refugee Day.” <https://medium.com/@JoeBiden/my-statement-on-world-refugee-day-fddb4abddfd5>.

[xv] “Closed Doors.” World Relief and Open Doors. <https://worldrelief.org/content/uploads/2020/07/Closed-Doors-Report_-Final.pdf>.

[xvi] “FINAL Jud Letter on Refugee PD.” <https://www.leahy.senate.gov/imo/media/doc/11.06.19%20FINAL%20Jud%20Letter%20on%20Refugee%20PD.PDF>.

[xvii] “Sen. Kamala Harris visits troops, refugee camp in Middle East” <https://abc7.com/politics/sen-kamala-harris-visits-troops-refugee-camp-in-middle-east/1885500/>.

[xviii] Stephen Rodrick, Mike Pence’s Refugee Problem. Rolling Stone, 01/25/2017. <https://www.rollingstone.com/politics/politics-features/mike-pences-refugee-problem-124345/>.

[xix] Voice for Refuge Scorecards: Kamala Harris. <https://www.voiceforrefuge.org/senate-scorecards/kamala-harris/>.

[xx] Jeff Stein, Kamala Harris’s immigration gamble. Vox Media, 09/01/2017. <https://www.vox.com/policy-and-politics/2017/11/1/16554958/kamala-harris-immigration-california>.

[xxi] House Vote 625 - Approves DREAM Act. Pro Publica, 12/08/2010. <https://projects.propublica.org/represent/votes/111/house/2/625>.

[xxii] “FINAL Jud Letter on Refugee PD.” <https://www.leahy.senate.gov/imo/media/doc/11.06.19%20FINAL%20Jud%20Letter%20on%20Refugee%20PD.PDF>.

[xxiii] Jeff Stein, Kamala Harris’s immigration gamble. Vox Media, 09/01/2017. <https://www.vox.com/policy-and-politics/2017/11/1/16554958/kamala-harris-immigration-california>.

[xxiv] Harris et al, Harris, Feinstein, Colleagues Call for a National Commitment to Refugee Resettlement on Third Anniversary of Trump’s Travel Ban. U.S. Senator Kamala Harris, 01/28/2020. <https://www.harris.senate.gov/news/press-releases/harris-feinstein-colleagues-call-for-a-national-commitment-to- refugee-resettlement-on-third-anniversary-of-trumps-travel-ban>.

[xxv] Stephen Rodrick, Mike Pence’s Refugee Problem. Rolling Stone, 01/25/2017. <https://www.rollingstone.com/politics/politics-features/mike-pences-refugee-problem-124345/>.